## <u>ዕንባችን ሲታበስ</u>

እንባዋ ነበር ዓባይ ለሚየ ኢትዮጵያ፣

ሲፈስ የኖረ ከወዲህ ወደዚያ፤

የዘመናት ህልም የአበሾች ቁጭት

የትወልዶች ዜማ የቅኔ የተረት፣

በመሪዎች ብልሃት በህዝቦችም ህበረት፣

ዓባይ ሊሆን ጉልበት፣

ዓባይ ሊሆን  ህብስት፣

አደንተባለልን የዳቦ ቅርጫት፡፡

ዕንባችን ሊታበስ ጀመርን ጉዛችን፣

አንድ አመት ሞላን -እንደዚህ አምሮብን፣

ደምቆ ውበታችን- ልቆ ህበረታችን ፤

ይቀጥላል ገና ጠንክሮ ክንዳችን፣

እውን እስከሚሆን  ትልቁ ግባችን ፡፡

የሃይል ምንጭ ማማ  ማራኪው ሰገነት፣

ለኢንዱትሪ እደገት ወሳኙ መሰረት ፡፡

የህዳሴው አሻራ በልማቱ ዙርያ፣

የአፍሪካ መመኪያ ፣

ልክ እንደ ዓድዋ ኣጥቢያ፣

የድሎች ማብሰርያ፡፡